# የግብር/ታክስ የክፍያ ጊዜ ስምምነት

# የአፈፃፀም መመሪያ

*የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን*

*ነሐሴ 2001 ዓ.ም.*

*አዲስ አበባ*

# የግብር/ታክስ የክፍያ ጊዜ ስምምነት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 30/2001

ባለሥልጣኑ ግብር ከፋዮች የክፍያ ግዴታቸውን መወጣት እንዲችሉ ተገቢነት ያላቸውን ሁኔታዎች በማመቻቸት ድጋፍና እገዛ ማድረግ የሚጠበቅበት በመሆኑ፣

የሚፈለግባቸውን ዕዳ በአንድ ጊዜ መክፈል ለማይችሉ ግብር ከፋዮች የተገደበ የክፍያ ጊዜ የመስጠት ተግባር ግልጽ የሆነ የአሠራር ስርዓት ተቀርጾለት ሁሉም ታክስ ከፋዮች ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ሊስተናዱ ስለሚገባ እና አሠራሩም ተጠያቂነትን የተላበሰ እንዲሆን ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1995 አንቀጽ 27፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 39፣ በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995 አንቀጽ 38 እንዲሁም በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995 አንቀጽ 35 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የግብር/ታክስ የክፍያ ጊዜ ስምምነት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 30/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

1. "የክፍያ ጊዜ ስምምነት" ማለት ግብር ከፋይ የግብር እና ወይም ታክስ ክፍያ ግዴታውን በአንድ ጊዜ ለመፈፀም ሳይችል ሲቀር ግብር ከፋዩና ባለሥልጣኑ ክፍያው ስለሚፈፀምበት ጊዜ እና ሁኔታ በተመለከተ የሚያደርጉት ስምምነት ነው።
2. "የግብር ዘመን" ማለት እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ያለው ጊዜ ወይም ግብር ከፋዩ ተፈቅዶለት የሚጠቀምበት የአንድ ዓመት የግብር ዘመን ነው።
3. "ግብር ከፋይ" ማለት በግብርና ታክስ አዋጆች መሠረት ግብርና ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ነው።
4. "ግብር/ታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ" ማለት በግብር/ታክስ አዋጆቹ መሠረት የተዘጋጀና ከግብር/ታክስ ከፋዩ የሚፈለገውን ግብር/ታክስ እንደዚሁም መቀጫ/ወለድ የሚያሳይ በተገቢው ባለሥልጣን የተፈረመ ቅጽ፣ ደብዳቤ፣ ወይም ማናቸውም ሰነድ ነው።

5. "ከአቅም በላይ" ማለት ከፍተኛ የተፈጥሮ ችግር ወይም ከባድ አደጋ ወይም ጥፋት ሲደርስ ወይም ግብር ከፋዩ ያለበትን የታክስ ዕዳ በተሟላ ሁኔታ መክፈል እንዳይችል የሚያደርግ ተጨባጭ ምክንያት ሲኖር ነው፡፡
6. "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡

## 3. <u>የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ የክፍያ ጊዜ ስምምነት መመሪያ በሚከተሉት ግብር ከፋዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፤

1. የግብር እና ወይም የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ለደረሳቸው፣
2. ጉዳያቸው በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ወይም በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ወይም በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እየታየ እያለ ወደውና ፈቅደው ክርክሩን አቋርጠው ጉዳዩ ከሚገኝበት አካል ስለማቋረጣቸው ከተሰጠ ማስረጃ ጋር የክፍያ ጊዜ እንዲሰጣቸው በጽሁፍ ላመለከቱ፣
3. ላልተከፈለ የግብር/የታክስ ዕዳ ለማዋል ንብረታቸው ከተያዘባቸው ወይም ንብረታቸውን ለመሸጥ ሀራጅ ከወጣ በኋላ ለመክፈል ፈቃደኛ ለሆኑ፣

## 4. <u>የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች</u>

ማንኛውም ግብር/ታክስ ከፋይ፡-

1. ቀደም ሲል የክፍያ ጊዜ ስምምነት የተሰጠው ሆኖ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግዴታውን ካልተወጣ፣
2. በማናቸውም የግብር እና የታክስ ዓይነቶች በማስታወቂያው ወቅት መክፈል ያለበት ግብር እና ታክስ ከሆነ፣
3. ለተመሳሳይ ዓመት በአንድ ውሳኔ ማስታወቂያ በድጋሚ የክፍያ ስምምነት የጠየቀ ከሆነ፣
4. የክፍያ ጊዜ የተጠየቀበት የዕዳ መጠን ከብር 15000 /አስራ አምስት ሺህ/ በታች ከሆነ፣
5. የግብር ወይም የታክስ ማጭበርበር የፈፀመ ስለመሆኑ ሪከርድ ያለበት ከሆነ፣ በጥፋቱ ተፀጽቶ ጥሩ ግብር ከፋይ መሆኑን ማረጋገጥ እስኪቻል ድረስ፣

የክፍያ ጊዜ አይሰጥም፡፡

## 5. የክፍያ ስምምነት የጊዜ ገደብ ስለመወሰን

1. የግብር ወይም የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው ግብር ከፋይ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች የሚፈለገው ጠቅላላ  የግብር ወይም ታክስ ዕዳ፡-

    1. ከብር 15,000-500,000ከሆነ እስከ 4 ወር፣
    2. ከብር 500,001-1,000,000 ከሆነ እስከ 8 ወር፣
    3. ከብር 1,000,001-1,500,000 ከሆነ እስከ 12 ወር፣
    4. ከብር 1,500,001-2,000,000 እና በላይ ከሆነ እስከ 18 ወር፣

 የክፍያ ጊዜ ገደብ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 6. በግብር እና ወይም ታክስ ከፋዩ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

1. በዚህ መመሪያ መሠረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት በሚገባባቸው የግብር ወይም/እና የታክስ ዕዳዎች ቢያንስ 25% /ሃያ አምስት በመቶ/ በቅድሚያ ክፍያ ተፈጽሞ ቀሪው ዕዳ ክፍያ እንዲፈጸም ስምምነት ለሚገባባቸው ወራቶች እኩል ተካፍሎ ክፍያው የሚፈጸም ይሆናል፡፡

2. የክፍያ ስምምነት ጥያቄ የቀረበው የግብር ወይም ታክስ ከፋይ ንብረት ወይም ሀብት ከተያዘ በኂላ ከሆነ በቅድሚያ ቢያንስ የግብር ወይም/እና የታክስ ዕዳውን 50% /ሃምሳ ከመቶ/ ከከፈለ ቀሪውን ዕዳ በ3 ወር እኩል ክፍያ እንዲያጠናቅቅ ስምምነት ይሰጠዋል፣

3. ጉዳዩ በፍርድ ቤት ወይም በፍርድ አፈፃፀም ላይ የሚገኝ ከሆነ ግብር ከፋዩ ባለሥልጣኑ  የግብር ወይም/እና ታክስ አሰባሰቡን አፈጻጸም ለመከታተል ያወጣቸውን ወጪዎች በሙሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ጋር በቅድሚያ መክፈል ይኖርበታል፡፡

4. ቅድሚያ ክፍያ ከተፈፀመ በኂላ ያሉት ቀሪ ክፍያዎች ላይ ስምምነቱ የሚታሰበውና የሚገባው ቅድሚያ ክፍያው ከተፈፀመበት ወር ቀጥሎ ባለው ወር የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

5. በዚህ መመሪያ መሠረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት የተገባበት የግብር ወይም/እና የታክስ ክፍያ በህጉ መሠረት መከፈል ከነበረበት ቀን ጀምሮ እስከ ተከፈለበት ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በግብር እና ታክስ ህጎች መሠረት ወለድ ይከፈልበታል፡፡

6. በማናቸውም የክፍያ ጊዜ ስምምነት ባለፈው የሩብ ዓመት በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ በዋለው ከፍተኛው የማበደሪያ ወለድ መጣኔ ላይ 25% ተጨምሮ ወለድ ይከፈልበታል፡፡

7. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) አፈፃፀም ወለድ የሚታሰበው ባልተከፈለው ወይም በሚቀረው ጠቅላላ የፍሬ ግብር፣ የወለድና የመቀጫ ድምር የገንዘብ መጠን ላይ ነው፡፡

## 7. ልዩ ልዩ ጉዳዮች

1. በጨረታ ለመሳተፍ፣ የንግድ ስራ ፈቃድ እድሳት አገልግሎት እና የከላውዶ አገልግሎት .... ወዘተ ለማግኘት የግብር አከፋፈል የምስክር ወረቀት /Clearance/ እንዲሰጠው በግብር ከፋዩ ጥያቄ ሲቀርብ የክፍያ ስምምነት ውል ስለመግባቱ እና በውሉ መሠረት በትክክል ክፍያ እየተፈፀመ ስለመሆኑ በሚመለከተው የስራ ሂደት በቅድሚያ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

2. በክፍያ ጊዜ ስምምነት ውሉ መሠረት ክፍያ የሚፈጸምበት ቀን በበዓላት ወይም በዕረፍት ቀናት ላይ ከዋለ ክፍያው በቀጣዩ የስራ ቀን መፈጸም አለበት፡፡

3. የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል በ3 ኮፒ ተዘጋጅቶ ዋናው ኮፒ ከማህደር ጋር ይያያዛል፣ 2ኛው ኮፒ ለግብር ከፋዩ ይሰጣል፣ 3ኛው ኮፒ ለክትትልና አፈፃፀም ለግብር አሰባሰብ፣ አወሳሰንና ክትትል የሥራ ሂደት ይተላለፋል፡፡

4. የክፍያ ጊዜ ስምምነት የገቡ ግብር ከፋዮችን የክፍያ አፈፃፀም ለመከታተል እንዲቻል በግብር አሰባሰብ፣ አወሳሰንና ክትትል የስራ ሂደት ቋሚ መዝገብ ተደራጅቶ ተገቢው ምዝገባ ይከናወናል፡፡ በታክስ ሥርዓቱ የመረጃ ቴክኖሎጂም እንዲያዝ ይደረጋል፡፡

5. ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ኗጉሜ የነሐሴ ወር አካል ሆኖ ይቆጠራል፡፡

6. የግብር አሰባሰብ፣ አወሳሰንና ክትትል የሥራ ሂደት እንዲሁም የደንበኞች አገልግሎት የስራ ሂደት ባለቤት የክፍያ ጊዜ ስምምነት ስለገቡ ግብር ከፋዮች ዝርዝር መረጃ ማለትም የክፍያ ስምምነት የተገባበትን የግብር ዓይነት፣ የግብር ዘመን፣ ፍሬ ግብር፣ መቀጫ እና ወለድ፣ በቅድሚያ የተከፈለ ገንዘብ መጠን፣ ስምምነት የተገባበት ቀን እና

የመክፈያ ጊዜ ያካተተ ሪፖርት በየወሩ እያዘጋጀ ለቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ ስራ አስኪያጅ እና ለግብር አሰባሰብና ክትትል ዳይሬክተር ይልካል፡፡

## 8. የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ አቀራረብ እና አፈጻጸም ሥርዓት

1. ለስራው አግባብነት ያለው ሠራተኛ /Case Worker/ የክፍያ ስምምነት ጥያቄ ይቀበላል፣ መርምሮ የስምምነት ውል በማዘጋጀት ይፈራረማል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት መፈፀም የማያስችል ከአቅም በላይ የሆነ ጉዳይ ሲገጥም ለስራው አግባብነት ያለው ሠራተኛ /Case Worker/ ጉዳዩን መርምሮ የውሣኔ ሃሣብ ለስራ ሂደት ባለቤት /Process Owner/ ያቀርባል፡፡

3. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4(1) የተመለከተው ቢኖርም የክፍያ ጊዜ ስምምነት ተሰጥቷቸው ግዴታቸውን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መወጣት ያልቻሉ ግብር ከፋዮች ማስረጃ ሲያቀርቡና በስራው ሂደት ባለቤት ማስረጃው ተቀባይነት ሲያገኝ ለመጨረሻ ጊዜ በአንቀጽ 6 መሠረት በድጋሚ የክፍያ ጊዜ እንዲራዘም ሊፈቀድ ይችላል፡፡

4. በአንቀጽ 4(1) የተደነገገው ቢኖርም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የሚፈለግባቸውን የግብር ግዴታ ወይም በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግዴታቸውን መወጣት ያልቻሉ ግብር ከፋዮች የሚያቀርቡት ምክንያት በቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ሲታመንበት ስራ አስኪያጁ በጉዳዩ ላይ ከኦኘሬሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ጋር በመመካከር በመመሪያው አንቀጽ 5 ከተመለከተው ጊዜ በላይ ተጨማሪ የክፍያ ጊዜ ገደብ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በዚህ ዓይነት የሚሰጠው የክፍያ ጊዜ ገደብ በምንም ምክንያት ከ3 ዓመት ሊበልጥ አይችልም፡፡

5. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) አፈፃፀም የቅርጫፍ ሥራ አስኪያጅ፣ የኦፐሬሽን ዘርፍ ም/ዋ/ዳይሬክተሩን ሳያማክር እስከ 2/ሁለት/ ዓመት ጊዜ መስጠት የሚችል ሲሆን፣ ከሁለት ዓመት በላይ እስከ 3 ዓመት ላለው ጊዜ ውሳኔ የሚሰጠው የኦፐሬሽን ዘርፍ ም/ዋ/ዳይሬክተር ነው፡፡

## 9. ግዴታን አለመፈፀም

በዚህ መመሪያ መሠረት የተሰጠውን የክፍያ ጊዜ ስምምነት ተጠቅሞ እዳውን ያላጠናቀቀ ግብር/ታክስ ከፋይ ያለምንም ተጨማሪ ማስጠንቀቂያ ንብረቱ ተይዞ እንዲሸጥ ይደረጋል፡፡

## 10. <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎች</u>

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ሌሎች መመሪያዎች እና ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 11. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ _______________ ቀን 2001 ዓ.ም.

መላኩ ፈንታ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ዋና ዳይሬክተር